# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ.ም.

## <u>በኢሬቻ በዓል በዜጎች ላይ የደረሰውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ኢሕአፓ ያወግዛል!</u>

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ግድያ ማካሄዱ በየጊዜው የተመዘገበ በመሆኑ ለማንም ስውር አይደለም። ባላፉት ሀያ አምስት የጥፋት ዓመታት በሸዋ፤ በወለጋ፤ በጎንደር፤ በሐረር፤ በባሌ፤ በጎጃም፤ በሲዳሞ፤ በአርሲ፤ በጎሞጎፋ፤ በትግራይ፤ በከፋ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች በአርሦ አደሮች፤ በነጋዴዎች፤ በሠራተኞች፤ በምሁራን በተማሪዎች ፤በክርስትና፣ በእስልምና እምነት ተከታይ ምእመናንና ፤ በነፃ ጋዜጤኞች ላይ በየጊዜው ያካሄደውና እያካሄደ ያለው ጭፍጨፋ ፤ እስራትና የማሳደድ ወንጀል ዛሬም በከፋ ሁኔታ በስፋትና በጥልቀት በመላው የአገሪቱ ክፍሎች ቀጥሏል። ከኃይል በመለስ አንዳችም ነገር የማይታየው ፋሽታዊውና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እሁድ መስከረም 22ቀን 2009ዓ.ም በቢሾፍቱ/ደበረዘይት ከተማ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ወግና ባህል መሠረት የኢሬቻን ዓመታዊ በዓል ለማክበር በተሰበሰቡ ዜጎች ላይ ያካሄደው ሰብአዊነት የጎደለው ጭፍጨፋ በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎች መገደላቸውና ቁጥራችው በውል ያልታወቀ መቁሰላቸው ተረጋግጧል። እስካሁን በህይወት መኖራቸውና አለመኖራቸው የማይታወቁም በርካታ ናቸው። ኢሕአፓ የወያኔ አገዛዝ ያደረሰውን ጭፍጨፋ አጥብቆ እያወገዘ ለሟች ወገኖችና ቤተሰቦች እንዲሁም የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ የተሰማውን ልባዊ ሀዘን ይገልጻል ።

ወያኔ ገና ሥልጣን ሲጨብጥ የጀመረው ተቃዋሚን የማጥፋትና የማፈን ዘመቻው አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን የጅምላ ጭፍጨፋውንም እያጧጠፈው ይገኛል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በጎንደርና በጎጃም ጭምር አገዛዙ የከፈተው ዜጎችን የማጥፋት ዘመቻ ዛሬም እንደቀጠለ ነው። በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ወጣቶች የዘረኛው አገዛዝ ደጋፊዎች ባለመሆናቸው ብቻ ያለምንም ወንጀል ከየመንገዱና ከመኖሪያ ቤታችው አየታፈኑ በመታሰር ላይ ሲሆኑ፤ በታሰሩትም ላይ የሚደርሰው አሰቃቂ ስየል ባስከፊ ሁኔታ በሰፊው ቀጥሏል።
ለአረመኔው የወያኔ አገዛዝ ሙሉ ድጋፍ በመስጠት ላይ የሚገኙት ባዕዳን መንግስታት በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የአገርና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ፣ የጦር መሳሪያና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለአገዛዙ መስጠታቸውን እንዲያቆሙ አጥብቀን እንጠይቃለን። በሚያቀርለቡት የጦር መሳሪያ አማካይነት ቡድኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እያካሄደ ስለሆነ ድርጊቱ በታሪክና በሕግ ፊት አንደሚያስጠይቃችው ልናስገነዝባችው እንድወዳለን።

የወያኔ አገዛዝ በሕዝባችን ላይ እያካሄደ ያለውን የሽብርና የሰቆቃ ዘመቻ ሁሉም ወገኖች እንዲያወግዙት ኢሕአፓ እየጠየቀ ተቃዋሚ ኃይሎችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያን ድርጊቱን ከማውገዝ ጀመሮ ይህንን አስከፊ አገዛዝ

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email** ESPIC@aol.com
**Website** www.eprp.com

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ለማስወገድ የሚደረገውን ሕዝባዊ ትግል ለማጠናከር የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪውን ያቀርባል። በሕዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው የግፍ ጭፍጨፋ ሊያበቃ የሚችለው የወያኔ አገዛዝ ከስረ መሰረቱ ሲፈነገል ብቻ መሆኑን አውቀን ይህን ሕዝባዊ ዓላማ በተባበረና በተጠናከረ ሕዝባዊ ትግል ከዳር እናድርስ እንላለን ።፡

ኢሕአፓ የሕዝብ ጠላት የሆነውን ወንጀለኛ ቡድን ገርስሶ ከስልጣን ለማስወገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረው አገራዊና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየመከረ ፓርቲው በግንባር ቀደምነት የሚያደርገውን የሞት የሽረት ተጋድሎ በበለጠ ቆራጥነት እንደሚቀጥል ዳግም ያረጋግጣል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አቸናፊ ነው!!